DeKalb County School District

Digital Dreamers

# Digital Dreamers የበይነመረብ ግንኙነት ተጠቃሚ ስምምነት
# SY2024 – 2025

የ DeKalb ካውንቲ ት/ቤት ዲስትሪክት በቅድመ መዋዕለ ህጻናት 12ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች የበይነመረብ ግንኙነት መሳሪያ ለቤተሰብ ይመድባል (SY 2024 – 2025)። የበይነመረብ ግንኙነት መሳሪያዎች የ DCSD (የDeKalb ካውንቲ ትምህርት ዲስትሪክት) ንብረት ሆነው ይቆያሉ እና ከድስትሪክቱ እና/ወይም ከዓመቱ የመሰብሰቢያ ሂደት ሲወጡ መመለስ አለባቸው።

መሳሪያው የሚሰጣቸው ተማሪዎች በዚህ ሰነድ ውስጥ የሚገኘውን መመሪያ እንዲሁም ባህሪይ እና የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በተመለከተ የወጡ የት/ቤት፣ መማሪያ ክፍል እና የት/ቤት አውራጃ ፖሊሲ እና አሰራር መከተል አለባቸው::

**ማነጋገር የሚችሉት ሰው፡** ጥያቄ ወይም ስጋት ካለዎት እባክዎ የት/ቤትዎን አስተዳዳር ያነጋግሩ::

## የኢንተርኔት ግንኙነት መሣሪያ የተጠቃሚ ስምምነት

**መሳሪያውን መቀበል**

<u>መሳሪያው ከመሰጠቱ በፊት ወላጆች እና ተማሪዎች ይህን ስምምነት ፈርመው መመለስ አለባቸው::</u>

**መሳሪያውን መመለስ**

በትምህርት አመቱ መጨረሻ ላይ መሳሪያው ለት/ቤቱ ይመለሳል:: በ DCSD ት/ቤቶች የሚሰጠው መሳሪያ ጥቅም ለሌላ ሰው አይተላለፍም እንዲሁም ተማሪው መሳሪያውን በሰጠው ት/ቤት መማር ሲያቆም ያበቃል::

በማንኛውም ምክንያት ከት/ቤቱ የተዛወረ፣ ያቋረጠ፣ የተባረረ ወይም የወጣ ተማሪ ባቋረጠበት/በወጣበት ቀን መሳሪያውን መመለስ አለበት::

መሣሪያውን መመለስ ያልቻለ ተማሪ ማንኛውንም መለዋወጫዎች የመሳሪያውን ሙሉ የመተካት ወጪ ለመክፈል ይገደዳል፣ እንዲሁም የክፍል ካርዶች፣ ግልባጮች፣ ዲፕሎማዎች ወይም የዕድገት ሰርተፍኬቶች እድሳት እስኪደረግ ድረስ ታግዶ ይቆያል።

**ብልሽት እና መጥፋት**

መሳሪያ ለተማሪ በተሰጠበት ወቅት ሆን ተብሎ ወይም በቸልተኝነት ቢበላሽ፣ ቢጠፋ ወይም ቢሰረቅ የተማሪው ወላጅ/አሳዳጊ በዚህ ሰነድ ላይ የተገለጸውን ቅጣት ይከፍላሉ::

**ቸልተኝነት**

የዲስትሪክቱ አስተዳደር በአንድ የትምህርት አመት መሳሪያው ብዙ ጊዜ ከተጎዳ የኢንተርኔት ግንኙነት መሳሪያን ሙሉ በሙሉ መተካትን ጨምሮ የእርምጃውን አካሄድ ይወስናል።

**ሀላፊነት ያለበት የመሳሪያ ተጠቃሚ**

ሁሉም በዲስትሪክት የተሰጡ መሳሪያዎች ተጠቃሚዎች በIFBGA ውስጥ በዲስትሪክት ፖሊሲ እና የአሠራር መመሪያዎች ውስጥ የተገለጹትን የሚጠበቁ ነገሮች መከተል አለባቸው:- *ሀላፊነት የተሞላው የ Enterprise Network, JD አጠቃቀም: የተማሪ ስኑ ስርአት/የተማሪ ስኑ ምግባር ደንብ* እና *JS: የተማሪ ቅጣቶች እና ክፍያዎች።* እነዚህን ደንቦች አለመከተል የስነስርአት ቅጣቶችን ያስከትላል:: ሁሉም የዲስትሪክት ፖሊሲዎች www.dekalbschoolsga.org ላይ ይገኛሉ።

እነዚህ መሳሪያዎች CIPA (የልጆች የኢንተርኔት ጥበቃ ህግ) የሚያከብሩ በትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት የተጣሩ እና ለማስተማሪያ አገልግሎት ብቻ የሚውሉ ናቸው። ተማሪ ከት/ቤት ቀጠና ውጪ በሚሆንበት ወቅት ስለመሳሪያው አጠቃቀም የቁጥጥር ሀላፊነት የሚወስደው ወላጅ ነው፡፡ ተማሪዎች መሳሪያውን በመጠቀም በማንኛውም ሰአት እና በየትኛውም ቦታ ተገቢ ያልሆነ ባህሪይ ማሳየት ወይም የተከለከሉ ነገሮችን ማግኘት አይችሉም ፡፡ ት/ቤት ውስጥ ወይም ውጪ ተማሪዎች መሳሪያውን ተገቢ ያልሆነ እንቅስቃሴ ለማድግ ከተጠቀሙበት የስነ-ምግባር ወይም የህግ ቅጣት ይከተላቸዋል፡፡

**ሚስጥራዊነት**

በዲስትሪክቱ የተሰጠ መሳሪያዎች የ DCSD ንብረት ሆነው ይቆያሉ። እንደዚሁም በመሣሪያው ላይ የሚደረግ ማንኛውም ነገር የግል አይደለም። ይህ ማለት የ DCSD ሰራተኞች በማንኛውም ቦታ በዲስትሪክቱ የተሰጠ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያን በመውሰድ አጠቃቀሙን ሊያዩ ይችላሉ፡፡

የDeKalb ካውንቲ ትምህርት ቤት ዲስትሪክት ሁሉንም የህፃናት የመስመር ላይ የግላዊነት ጥበቃ ህግ (**COPPA**)፣ የህፃናት የኢንተርኔት ጥበቃ ህግ (**CIPA**) እና የቤተሰብ ትምህርት መብቶች እና ግላዊነት ህግ (**FERPA**) ሁሉንም ገፅታዎች ይቀበላል።

የDeKalb ካውንቲ ትምህርት ቤት ዲስትሪክት የተማሪን የቤት ኔትወርኮች፣ መሳሪያዎች ወይም የበይነመረብ ግንኙነት አይቆጣጠርም። ዲስትሪክቱ በዲስትሪክቱ የተሰጠ መሳሪያ አጠቃቀም ይቆጣጠራል፡፡ በተጨማሪም DCSD ከዲስትሪክቱ የተሰጡትን መሳሪያዎች፣ መሳሪያው በሚጠፋበት ወይም በሚሰረቅበት ጊዜ የሚገኙበትን ቦታ ይከታተላል።

**ወርሃዊ የመሳሪያዎች አጠቃቀም**

የDeKalb ካውንቲ ትምህርት ቤት ዲስትሪክት መሳሪያዎችን በየወሩ ይቆጣጠራል። ዲስትሪክቱ አነስተኛ አጠቃቀም ካስተዋለ ፣ ት / ቤቱ ምን ዓይነት እርዳታ መስጠት እንደሚችል ለማየት ትምህርት ቤቱ ወላጆችን ያነጋግራቸዋል፡፡ አጠቃቀሙ ዝቅተኛ ከሆነ ወይም ተቀባይነት ያለው የአጠቃቀም ስምምነት ከተጣሰ ድስትሪክቱ አንድን ቤተሰብ መሳርያውን እንዲመልስ የመጠየቅ መብቱ የተጠበቀ ነው።

**ለመሳሪያ ጉዳት፣ ኪሳራ ወይም ስርቆት ቅጣቶች**

ለተማሪው በተሰጠበት ጊዜ መሣሪያው እና/ወይም መገልገያዎቹ ከጠፉ ወይም ከተሰረቁ፣ ሆን ተብሎም ይሁን በቸልተኝነት ተማሪው እና ወላጅ/አሳዳጊ የሚከተሉትን ክፍያዎች የመክፈል ኃላፊነት አለባቸው፡

**የኢንተርኔት ግንኙነት መሣሪያ መተካት**

| | |
|---|---|
| **የጠፉ/የተሰረቀ/ከጥገናው በላይ የተጎዳ** | • ሙሉ የመተካት ክፍያ (ለቼክ አውት እንደተገኘው መሣሪያ ላይ በመመስረት $90.00) |
| **የሚጠገን-ጉዳት** | • ጥገና አማራጭ መሆኑን ለማወቅ የተበላሹ መሳሪያዎች በDCSD ቡድን ይገመገማሉ። ከመጠገን በላይ ከተበላሸ ሙሉ ምትክ ክፍያ ያስፈልጋል። ከላይ ይመልከቱ፡፡ |

**የመሳሪያ ሙሉ መተኪያ ክፍያ የሚያካትተው መሳሪያውን፣ ሁሉንም ተያያዥነት ያላቸው እቃዎች፣ የሶፍትዌር ፈቃድ እና መጫኛን ነው፡፡*

**የስርቆት:**

መሳሪያው ለተማሪው በተሰጠበት ወቅት ከተሰረቀ ተማሪው፣ ወላጅ/አሳዳጊ የሚከተሉት ሀላፊነቶች አሉባቸው:

- የትምህርት ቤት አስተዳደርን ማሳወቅ
- የፖሊስ ዘገባ ማቅረብ
- ሙሉ ምትክ ክፍያ መክፈል

**ከት/ቤቱ በሚዛወሩበት/በሚወጡበት ጊዜ መሳሪያን ወይም መለዋወጫዎችን መመለስ አለመቻል:**

መሳሪያን ወይም ማናቸውንም መለዋወጫዎችን ሳይመልስ የሚዘዋወር ወይም የሚለቅ ተማሪው የኢንተርኔት የግንኙነት መሣሪያ ሙሉ ምትክ ክፍያ የመክፈል ሃላፊነት አለበት።

## <u>የወላጅ ፈቃድ መስጫ እና ነጻ ማድረጊያ</u>

ከስር በመፈረም በዚህ ሰነድ ውስጥ የሚገኙትን መመሪያዎች ማንበብዎትን እና መረዳትዎን እንዲሁም ለተማሪዎች መሳሪያ መስጠቱን መቀበልዎትን ያረጋግጣሉ፡፡ የበይነመረብ ግንኙነት መሳሪያ የDCSD ንብረት እንደሆነ እና ከዲስትሪክት እና/ወይም ከዓመቱ የመሰብሰብ ሂደት ሲጠናቀቅ መመለስ እንዳለበት ተረድተዋል። ተማሪው መሳሪያውን በሚይዝበት ወቅት መሳሪያው እና ተያያዥነት ያላቸው እቃዎች ላይ ለሚደርስ መበላሸት፣ መጥፋ ወይም መሰረቅ ሀላፊነት እንደሚወስድ ተረድተዋል እንዲሁም በዚህ ሰነድ ላይ የተገለጸውን የገንዘብ ቅጣት ለመክፈል ተስማምተዋል፡፡

ከትምህርት ቤት ውጭ በሚሆኑበት ጊዜ የተማሪውን የመሳሪያ አጠቃቀም ለመቆጣጠር ብቸኛው ሃላፊነት የእርስዎ እንደሆነ እና መሣሪያው ለትምህርታዊ ዓላማዎች ብቻ የሚያገለግል መሆኑን ተረድተው ተስማምተዋል። ተማሪዎች መሣሪያውን ተገቢ ላልሆኑ ወይም ለተከለከሉ ተግባራት ከተጠቀሙ የዲሲፕሊን እርምጃ እንደሚወሰድባቸው ተረድተዋል ፡፡

እርስዎ እና ተማሪዎ የDeKalb ካውንቲ ትምህርት ቤት ዲስትሪክት አግባብ ባልሆነ አጠቃቀም፣ በስህተት አጠቃቀም፣ በመነካካት፣ በጠለፋ ወይም በመሣሪያ ማበላሸት ምክንያት ሆን ተብሎ ወይም ባልታሰበ ጉዳት ተጠያቂ አለመሆኑን ይስማማሉ። ማንኛውም የ DeKalb ካውንቲ ት/ቤት ዲስትሪክት የበይነመረብ ተቀባይነት አጠቃቀም ስምምነትን የማያሟላ ማንኛውም ተጠቃሚ ተማሪ በአከባቢው የት/ቤት አስተዳደር ቅጣቶች እርምጃዎች ይወሰዳል። የተማሪ ህግ መጣስ ጥቅሞችን የማግኘት መብትን ከማሳጣድ እና ከማቋረጥ ባሻገር ተገቢ የስነ-ምግባር እርምጃ ሊያስከትል ይችላል፡፡

**የወላጅ/አሳዳጊ ስም**

**(እባክዎ ይጻፉ):** ______________________________________________

**ወላጅ/አሳዳጊ**

**ፊርማ:** ______________________________________________ ቀን: ______________

DeKalb County School District

Digital Dreamers

**<u>የተማሪ ስምምነት እና ፊርማ</u>**

1. ለት/ቤት የተሰጠውን መሳሪያዬን እከባከባለሁ፡፡
    a. ጉዳትን ለመከላከል ሶኬቶች እና አገናኝ ገመዶች መሳሪያው ላይ በጥንቃቄ መሰካት አለባቸው፡፡
    b. መሳሪያዎች በተከፈተ መቆለፊያ፣ መኪና ወይም በማንኛውም ክትትል በሌለበት ቦታ መተው የለባቸውም።
    c. ማንኛውም የሶፍትዌር/ሀርድዌር ጉዳዮችን በ Incident IQ – የተማሪ የእርዳታ ዴስክ ፖርታል በኩል ያሳውቁ፡፡
    d. መሳሪያውን በማይጠቀሙበት ወቅት ጥበቃ በሚደረግለት፣ ቁጥጥር የሚደረግበት ሙቀት ባለበት ሁኔታ ውስጥ ያስቀምጡት፡፡
2. ት/ቤት የሰጠኝን መሳሪያ ለሌላ ሰው በፍጹም አላውስም፡፡
3. ምግብ እና መጠጦች ከመሣሪያዬ ራቅ አደርጋለሁ።
4. የእኔንም ሆነ በማንኛውም የት/ቤት ውስጥ የተቀመጠ መሳሪያን አልበታትንም፣ ጄይልብሬክ ወይም ሀክ አላደርግም፡፡
5. በመሳሪያዬ ላይ ምንም አይነት ጥገና ለማድረግ **አልሞክርም።**
6. ት/ቤቱ የሰጠውን መሳሪያ አብሮት በተሰጠው መያዣ ብቻ በመያዝ ጥንቃቄ አደርግለታለሁ፡፡
7. ት/ቤቱ የሰጠውን መሳሪያ ት/ቤት፣ ቤት ውስጥ ወይም በማንኛውም ቦታ  የምጠቀመው ተገቢ በሆነ እና የት/ቤቱን ደንብ ባከበረ መልኩ ነው፡፡ መሳሪያዬን አግባብ ባልሆነ መንገድ ከተጠቀምኩ በትምህርት ቤቴ የዲሲፕሊን እርምጃ ሊወሰድብኝ ይችላል።
8. ትምህርት ቤት በተሰጠው መሳሪያ ላይ ማስዋቢያዎችን (እንደ ተለጣፊዎች፣ ማርከሮች፣ ወዘተ) **አላስቀምጥም።** ት/ቤት በሰጠው መሳሪያ ላይ የሚገኝ የሲሪያል ቁጥር መለጠፊያን አልጥም/አላበላሽም፡፡
9. በት/ቤት የተሰጠው መሣሪያዬ በማንኛውም ጊዜ ያለማስታወቂያ ለምርመራ እና ቁጥጥር ተጋላጭ እንደሆነ ተገንዝቤያለሁ። **<u>መሳሪያው</u> ላይ የምሰራው ወይም መሳሪያውን የማደርገው ነገር ሁሉ ሚስጥር አይደለም፡፡**
10. የእኔን የይለፍ ቃል ለመምህር ወይም ከት/ቤት ለመጣ አዋቂ ሰው ወይም ለእኔ ወላጅ/አሳዳጊ ካልሆነ በስተቀር ለሌላ ሰው አልሰጥም፡፡
11. የበይነመረብ ግንኙነት መሳሪያ የDCSD ንብረት እንደሆነ እና ከዲስትሪክቱ ሲወጣ እና/ወይም የአካዳሚክ ትምህርት አመት ሲያልቅ መመለስ እንዳለበት እረዳለሁ።
12. መሣሪያዬን ብጎዳ ወይም ከጠፋብኝ ወይም ከተሰረቀ መሣሪያውን የመተካት ወጪ እንደሚኖርብኝ አውቃለሁ።

**በመሣሪያ ተጠቃሚ ስምምነት እና በተማሪው ስምምነት ውስጥ በተቀመጡት ደንቦች እስማማለሁ።**

**የተማሪ ስም (እባክዎ ይጻፍ):** ____________________________________________

**የተማሪ ፊርማ፡-** ______________________________________________________ ቀን: ______________